# ልብ ስጠኝ ያአላህ

የዕለት ተግባሬን ውሎዬን መዘንኩት

መች ነው ነፍስያዬን ሳልበድል የዋልኩት

ደግሞ ያለማፈሬ እያወቅኩት ውስጤን

ምህረት መለመኔ አድርጼ የልቤን

ወንጀል ሳብሰለስል ልቤ ውስጥ አምቄ

ሰው እንዳያውቅብኝ በጣም ተጠንቅቄ

እቤት የኔ ነገር ዬት ይሆን መግብያዬ

በቀኝ ወይ በግራ መቆሚያ ስፍራዬ

ያአላህ ይገርማል የትዕግስትህ ስፋት

ከአዛብ አውጥተህ ታስገባለህ ጀነት

እባክህ ጌታዬ አንተው ይቅር በለኝ

ከጥፋት የማላርፍ መቼም ወላዋይ ነኝ

ታዲያ ምኑ ላይ ነው የኔ እስልምና

በወንጀል ውስጥ ነኝ አልጸዳሁም ገና

ምህረትህን አልበሰኝ ኃጢያቴን ፋቅና

አድነኝ ያአላህ ከሰይጣን ፈተና

ሐምዱ ኢድሪስ (የህሊና ዕረፍት)